


የግል መኪና መንገድ

የህዝብ ትራንስፖርት መንገድ

አያሎን መንገድ ቡና አይነት መስመር

የባቡር ሃዲድ

የብስኪሌት መንገድ


በከተማ መሃል ያለ መንገድ ለህዝብ ትራንስፖርትም የሚውል

እኛ የቆምነው ለናንተው ነውና ጥያቄዎቻችሁን ይዛችሁ ኑ ወደ እኛ
የሉድ ከተማ ማዘጋጃ ቤት ii.muni.lod የሉድ ኤኮኖሚ calcalitlod.co.il
*የስልክ ቁጥር 072 2211599

# በፍጥነት ከተማ

## አዲስ ደረጃውን የጠበቀ ትራንስፖርት እንገነባለን

## ፈጣን በከተማ ፕሮጀክት ወደ ሉድ ከተማ እየገሰገሰ ነው




*8541 ayalonhw.co.il | *8787 | 106

# በፍጥነት ከተማ

*አዲስ ደረጃውን የጠበቀ ትራንስፖርት እንገነባለን

ለተወደዳችሁ የሉድ ከተማ ነዋሪዎች በሙሉ

ከሌላው ዓለም መልካም ተሞክሮና ጥሩ ልምድ በመነሳት በአውራ ጎዳና መንገዶቻችን ላይ የትራፊክ መጨናነቅን ለመ ቀነስ በግልና በቤት መኪኖች ከመጠቀም ይልቅ በህዝብ የጋራ ትራንስፖርት የመንቀሳቀስን ልምድ ለማበረታታት የሉድ ከተማ ማዘጋጃ ቤት ፍጥኖ በከተማ ተብሎ የሚጠራ አዲስ ተቋም በመገንባት ላይ እንገኛለን የሉድ ከተማ ማዘጋጃ ቤት ከሃሄብራ ሃከልከሊት ሉድ (የሉድ ማህበረሰብ ኤኮኖሚ ድርጅት) ጋርና ከሚስራድ ሃታህቡራ ቨነቲቬ አያሎን (የአያሎን ጎዳና መስመሮች መንገድ ትራንስፖርት) መስሪያ ቤት ጋር በመተባበር የፈጥኖ በከተማ ተቋማችንን ሰፊ ዓቅድና ፕሮግራም ዘርግተን በመንቀሳቀስ ላይ ነን

የዚህ ተቋም ዓላማ ፤ የቴላቪቭ ሜትሮ ፖሊን የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎትን ቅርጫፍ በመላው ሃገሪቱ መሃል ከተሞች ማስፋፋት ነው

ፈጥኖ በከተማ ተቋም ደረጃውን የጠበቀ አዲስ የማይቋረጥ የሜትሮፖሊን ቅርንጫፍ የሆነ የጋራ የህዝብ መገልገያ ትራንስፖርትን አመቺና ውጤታማ በሆነ መልኩ ቀርጾና አርቅቆ በስራ በመተግበር ላይ ይገኛል

በዕቅዱ መሰረትም በሉድ ከተማ ውስጥ -ዮሴፍታል፤ሃቲቫትይፍታህ፤ዳቪድሃሜለህ፤ሃነሲሄርጸል፤ከጺንዬልሰንና አባሂለ ልሲልቨር ጎዳና የህዝብ መገልገያ መንገድ ትራንስፖርት አገልገሎቶችን ዘርግቶ በስተመጨረሻም የሄርጸል ጎዳና የመጀመ ሪያው ደረጃ ስራው ሙሉ በሙሉ መጠናቀቁን ባክብሮትና በታላቅ ትህትና እንገልጻለን

ፈጥኖ በከተማ ተቋም እነዚህን የህዝብ የጋራ መገልገያ የትራንስፖርት ምመስመሮች ሲገነባ የከተማዋን ነዋሪዎችና የጎብኚዎቿን ምቾት በሚጠብቅ መልኩ እንዲሆን የተቻለውን ሁሉ ጥረት በማድረግ በተግባርም እይሰራ ይገኛል ስለሆነም የከተማዋ መነሻና መድረሻ መንገዶች ጊዜን ቆጣቢ ያካባቢ ጽዳትና ንጽህና የአየር ብክለትን የሚያስወግድ የትራፊክ መጨናነቅን በመቀነስ የህዝብ የጋራ ትራንስፖርት የመጠቀም ልምድን በሚያዳብርና በሌሎችም ጉድዮች ላይ ሰፊ ጥናት የተደረገበት ፕሮግራም ነድፎ የከተማዋን ነዋሪዎችሊያሳትፍ የሚችል ጥሩ ስራ በመስራት ላይ ይገኛል በዚህ ፕሮግራም መሰረትም የከተማዋን ነዋሪ ህዝብ በቀጥታ የሚያሳትፍ ትልቅ ስብሰባ ጠርተን ህዝቡን እንጠብቃለን በስብሰባው ፈጥኖ በከተማ ተቋም ራሱን ብግልጽ አሳውቆ ዓላማና ግቡንም ለህዝብ ዘርዝሮ በይፋ የሚያቀርብ ይሆናል በዚህ አጋጣሚም የህዝቡ ቀጥታ ጥያቄና መልሶች ይስታናገዳሉ ከተሰብሳቢው የሚፈልቁ መልካም ለውጥን የሚያመጡ አዳዲስ ፍሬያማ ሊሆኑ የሚችሉ ጥሩ ጥሩ ሃሳቦች ለውይይት ቀርበው የፕሮግራሙም አካል ሆነው እንዲካ ተቱ ይሆላሉ

ለዚህ በከተማችን እየተካሄደ ባለው አዲስ የመለወጥ ግስጋሴ ቋሚ ምሶሶ ሆናችሁ ከተማዋን ለማሳደግ የበኩላችሁን ድርሻ በማበርከት ከፈጥኖ በከተማ ተቋም ጎን እንድትሆኑበመተማመን ለከተማዋ እድል በር ከፋቻንድትሆኑ ትብብራ ችሁን በታላቅ ትህትናና በታላቅ አክብሮት እንጠብቃለን ተሳትፎአችሁም እንዳይለየን ከወዲሁ አደራ እንላለን

አክባሪያችሁ
ጠበቃ ያኢር ረቢቦ
የከተማችን ከንቲባ

## የናንተዋ የሉድ ከተማ ትሃድሶ

ፈጥኖ በከተማ ፕሮጀክት ባወጣው ፕሮግራም መሰረት 8 ኪ.ሜ ርቀት የጋራ የህዝብ መገልገያ ትራንስፖርት መስመሮችና 2.5 ኪ.ሜ የብስክሌት መንገዶች ይዘረጋሉ.

ከ እሁድ 7/6/2020 ጀምሮ ለሶስት ዐመታት ሊዘልቅ የሚችል በፕሮጀክታችን እንደሚከተለው በየፈርጁ የተቀረጹና ሊተገበሩ የተዘጋጁ ስራዎች - በስፐሪላት ሃሃሽማል አደባባይ መሃል በራምሌ ዮሴፍታል ጎዳና በሉድ ሃቲቫት ሃይፍታህና ዳቪድ ሃሜለህ መንገዶች እስከ (መገናኛ) ጾሜት ሃነሲ የሚደርሰው 3 ኪ.ሜ ይሆናል.

.በሚቀጥሉት ወራቶች በሄርጸል ጎዳና በስተሰሜን በኩል ከሚገኘው የፓልማህ አደባባይ እስከ ሚብጻ ዮናታን ድረስ የሚዘረ ጋው ርዝመቱ እስከ 300 ሜትር ይሆናል

## የአሰራር ሂደትና ቅደም ተከተል

- **ስራው ለነዋሪዎችና ለንግዱ ዘርፍ እንደሚመች ሆኖ በየፈርጁ ተከፋፍሎ ይከናወናል.**
- የትራፊክ መስመሮች መጓጓዣዎች እንዲተላለፉ ይሚያስችሉ ይሆናሉ.. ቁጥራቸው የሚቀንስም ቢሆን እንኳን ይህ በመሆኑ ጨርሰው የሚዘጉ መንገዶች አይኖሩም
- **የእግረኛ መሄጃ መንገዶችም ስራው ተጀምሮ እስኪያልቅ ክፍት ሆነው ወደ መኖሪያ በቶችና ወደ መገበያያ መተላለፊያ መንገዶች የሚሰጡት አገልግሎት እንደተጠበቀ ይቀጥላል**
- **ከእሁድ እስከ ሃሙስ ድረስ የመንገድ ስራዎቻችን በተከታታይ ይከናወናሉ የዐርብ ቀን ስራችን ግን በየሳምንቱ አንድ አርብ እየታረፈ የሚካሄድ ይሆናል**
- **በለሊት የመንገዶቻችን ስራዎች ሊካሄዱ ይችሉ ይሆናል ይሄንን በተመለከተ ቀደም ብለን በተለየ ማስታወቂያ የምናሳ ውቅ ይሆናል**

## የፕሮጀክቱ ይዘት

- የህዝብ ትራንስፖርት መንገድ መዘርጋት
- የቢስኪሌት መንገድ መዘርጋት
- መሰረተ ልማት ማደስና ማሻሻል
- አውቶብስ መጠባበቂያ ፌር ማታና አካባቢውን ማሻሻል
- የአካባቢውን እይታ ማሳመር
- መንገድ ላይ ያሉ መገልገያዎች ማደስ
- የመንገድ መብራቶች ማደስና ማሻሻል
- የዳርቻ መንገድና ወለሉን ማደስ

የሉድ ከተማ ማዘጋጃ ቤት ሮሆቭ ዳቪድ ሃሜለህ ከአሁን ቀደምና በኋላ






נתיבי איילון תחבורה מתקדמת לישראל | *8541 ayalonhw.co.il | משרד התחבורה והבטיחות בדרכים *8787 | כלכלית לוד חולמים יוזמים מבצעים | עיריית לוד ושבו בנים לגבולם | 106 מוקד שירות עירוני

נתיבי איילון תחבורה מתקדמת לישראל | *8541 ayalonhw.co.il | משרד התחבורה והבטיחות בדרכים *8787 | כלכלית לוד חולמים יוזמים מבצעים | עיריית לוד ושבו בנים לגבולם | 106 מוקד שירות עירוני